

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order

www.ethiopianorthodox.org

## አዋልድ መጻሕፍት

አዋልድ መጻሕፍት ማለት ጥሬ ትርጉሙ «የመጻሕ ፍት ልጆች» ማለት ነው:: «አዋልድ ተብለሙ የተጠሩበትም ምክንያት አሥ ራው መጻሕፍት ስላሉ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት መሠረታ ውያን የሆኑትን ንባብ እንጂ ትርጓሜ፣ ጥሬ ዘር እጂ ትንታኔ የሌላቸውን፣ ቁጥራቸው ሰማንያአንድ የሆኑትን አምላካ ውያት መጻሕፍት አሥራው /ሥሮች-መሠረቶች/ መጻሕፍት እንላቸዋለን::

እነዚህን አሥራው መጻሕፍት የሚተረጉሙ፣ የሚተነትኑ፣ ምሥጢሩን አራር ቀው ትርጓሜውን አቃንተው የሚያቀርቡ፣ በነቢብ የተገለ ጠውን በገቢር፣ በትምህርት የተሰጠውን በሰው ሕይወት የሚያሳዩ መጻሕፍት ደግሞ አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ:: ልጅነታቸው ለአሥራው መጻሕ ፍት ነው:: ልጅ ከአባቱ አብራክ ከእናቱ ማኅፀን ተከፍሎ፣ ወላጆቹን መስሎ ወላጆቹን አኽሎ እንዲወጣ እነዚህም በምሥጢርም በእምነትም በሥር ዓትም የአሥራውን መጻሕፍት ሥርና መሠረት ይዘው እነርሱን አኽለው እነርሱን መስለው ተገኝተዋልና«አዋልድ» ይባላሉ ::

ለአዋልድ መጻሕፍት ምስክራቸው አሥራው መጻሕ ፍት ናቸው:: በምሥጢርም በትምህርትም ከአሥራው መጻሕፍት የሚቃረን መጽሐፍ ከአዋልድ መጻሕፍት ተራ አይገባም:: ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ የሚለይ ወንጌልን ከሰበክንላቸው ወን ጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን :: /ገላ.1:8/ በሚለው ቃል ታሥሯልና:: ለአሥራው መጻሕፍት ማንቶታቸው አዋልድ መጻሕፍት ናቸው :: በገመድ ያለ የኤሌትሪክ ኃይል በጥጥ ያለ ዘይት የሚፈኩት የሚታዩት የሚገለጡት በአምፖል በማ ንቶት ሲበሩ ነው:: በአሥራው መጻሕፍት የሚገኝ ጥበብ ትምህርትና ምሥጢር የሚፈ ካው የሚረዳው በአዋልድ መጻሕ ፍት ተፍታቶ ተብራርቶ ተራቅቆ ሲታይ ሲገለጥ ነው::

አዋልድ መጻሕፍት የአሥራው መጻሕፍት ልጆች መሆናቸውን በሶስት መልክ ማየት ይቻላል ::

1. በዓይነታቸው

አሥራው በጸሕፍት የተሰኙ ሰማንያ አሐድ መጻሕፍ በይዘታቸው

1.1 ሕግ /ለምሣሌ አምስቱ ብሔረ ኦሪት/

1.2 ታሪክ /ለምሳሌ መ ጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ/

1.3 ጥበብ፣ቅኔ፣ ጸሎት ትምህርት /ለምሳሌ መዝሙ ረ ዳዊትና ጥበበ ሰሎሞን/

1.4 ትንቢት /ለምሣሌ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ኤርም ርያስ፣ ዳንኤል /ተብለው ይከ ፈላሉ:: አዋልድ መጻሕፍትም በዚሁ መልክ ተከፍለው ሊጠኑ ይችላሉ::

ሕግ :- ስለ ቤተ ክርክስ ቲያን፣ ስለ ክርስቲያናዊ ኑሮ ወዘተ ሕግና /ሥርዓት/ የወጣባቸው መጻሕፍት አሉ /ለምሳሌ ፍትሐ ነገ ሥት /

ታሪክ:- የቅዱሳንን ሕይወት ገድል ተመምራት የሚናገሩ መጻሕፍት /ለምሣሌ ተአምረ ማርያም ገድለ ተክለሃይ ማኖት /

ጥበብ፣ ቅኔ፣ ጸሎት ትምህርት:- አበው የጸለዩትን ጸሎት ያመሰገኑበትን ምስጋናና ቅዳሴ ተንትነው አመስጥረው ያስተማ ሩትን ትምህርት የያዙ መጻሕፍት አሉ:: /ውዳሴ ማርያም ጸሎተ ማርያም ውዳሴ አምላክ ሃይማኖተ አበው /

ትንቢት:- እግዚአብሔር መን ፈስ ቅዱስ ስለ ወደፊቱ የገለ ጠላቸውን ትንቢት የጻፈባው መጻሕፍት አሉ::

2 ባለቤታቸው

የቅዱሳት መጻሕፍት ባለ ቤት ቤተ ክርስቲያን ናት :: የቤተ አይሁድ /የቤተ መቅደስ/ ወራሀ ቤተ ክርስቲያን እንደመ ሆንዋ መጠን የብሉይ ወራሀ ሐዲስ የኦሪት ወራሀ ወንጌል ናቸው:: የወንጌልም የሐዲስም ባለቤት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት ::እግዚአብሔር በደሙ የዋጃት በምድር የእግዚአብሔር እንደራሴ ናትና:: /የሐዋ 20-28/ ሐዋርያት ወንጌልንም መልዕክትንም የጻፉት ለቤተ ክርስቲያን ነው:: በሰዎች ስም የተጠሩት መጻሕፍትም ቢሆኑ አንድም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስበለዚያም አገ ልጋዮች ነበሩ:: /1ቆሮ 1-2 ገላ 1-21 ፊልጵ 1-1 1ተሰ 1-2 1ፊል1/:: የአዋልድ መጻሕፍትም ባለቤት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ጸሐፊዎቻቸው ልጆቿ ናቸውና:: ለትርጉማቸውም ለታሪነቸውም ለምሥጢራ ቸውም መጠየቅ ያለባት እርስዋ ናት ::

2. ቅድስናቸው

አሥራውንም ሆነ አዋልድ መጻሕፍትን ያስጻ ፈው መንፈስ ቅዱስ ነው:: አባትንም ልጅንም የሚያስገኝ መንፈስ ቅዱስ የአሥራውን መጻቅፍት ደራስያን እንደ መረጠ እንደሾመ እንደቀደሰ ከስህተትም እንደጠበቀ ሁሉ የአዋልድ መጻሕፍትንም ደራስያን መርጧል ሾሟል ቀድሷል ከስሕተትም ጠብቋል:: የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህ ርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅ ናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል /2ጢሞ 3-16/ በማለት ሐዋርያው ቅድስ ጳውሎስ እንደተናገረ አዋልድ መጻሕ ፍትን ያስጻፈው መንፈስ ቅዱስ /የእግዚአብሔር መንፈስ/ በመሆኑ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት ደጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማሉ:: በመሆኑም አሥራውንና አዋልድ መጻሕፍትን በአንድነት «ቅዱሳት መጻሕፍት» ብለን እንጠራቸዋለን::

አንዳንድ ሰዎች «መጽሐፍ ቅዱስ»ን እንደ አንድና ብቸኛ መጽሐፍ በመቁጠር ሌሎች የቤተክርስቲያን መጻሕ ፍት «አፖክሪፖ» ማለት ግን በግሪኩ ቋንቋ «ስውር ሽሽግ ድብቅ» ማለት ነው:: ይህም ለጥንቆላ መጻሕፍት የሚሰጥ ስም እንጂ ለቅዱሳት መጻሕፍት የሚቀጸል አይደለም::

እያንዳንዱ መጽሐፍ /ሰማንያ አሃዱ/ በየራሳቸው የተጻፉ የተገኙና በቀኖና የተያዙ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ተብለው ተጠቃለው በአንድ ሰው በአንድ ጊዜ እና በአንድ ስፍራ አተጻፉ አይደሉም :: እያንዳንዱ በየራሱ ተጽፎና በየራሱ ተመዝግቦ በቤተ ክርስቲያን በመሆኑም እነዚህ የአዋ ልድ መጻሕፍት ጸሐፍት በእው ነተኛ መንፈስ ተመርተው እውነትን ጽፈዋልና እነርሱም ሆኑ መጽሐፋቸው ቅዱሳን ናቸው ብለን እናምናለን:: የቅዱሳት መጻሕፍቱ የአስረጅነት ሥልጣን (Authenticity) ከሚመነጭበት መሠረት አንዱም የጸሐፍቱ ብቃት ነው::

**ለበቀኖናቸው (Canonic Au thenticity )**

ቀኖና የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን መጠን (Standard) ማለት ነው:: በቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ቀኖና ማለት ደግሞ አንድን መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን መሆን ያለመሆኑን ለመለየት በቤተክርስቲያን ጉባኤ የሚመ ዝገበት ሥርዓት ነው:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የቅዱሳት መጻሕፍትነት ሥልጣን ያገኙት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ወንጌልን ሲያስተምር የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እየጠቀሰ የትንቢቱን መፈጸምና የሱባኤ ውን መድረስ እየነገረ ነበር:: ሐዋርያትም ስለ ጌታችን ሲያስተ ምሩ «ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እሱ የጻፉት » እያሉ ነበር:: /ዩሐ 1-46/:: በመቀጠልም አርባ ዕቱ ወንጌል በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ተመዝግበው በይፋ ቅዱሳት መጻሕፍት መሆናቸው እየታወቀ መጣ:: በሁለተኛው መ/ክ/ዘመን የነበረው ሰማዕቱ ዩስጢኖስ (Justin the martyr) በሮም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ጊዜ የነቢያት ትንቢትና (Memories of The Apostles ) /የሐዋርያት ማስታወሻ ስለ ጌታችን / ሲነበብ ማየቱን ገልጧል:: /The Bible Through the Ages, Readers Digest Itd, p, 203)

ለመጀመሪያ ጊዜ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን በሚል ቅድሳት መጻሕፍትን የከፈለውና በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ውስጥ ሁለቱንም አካትቶ የገለጠው የሊዮን (Lyöns) ሊቀ ጳጳስ ሄሬኔዎስ ነበር:: ሄሬኔዎስ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የምናገኘውን አርባዕቱን ወንጌል በአራቱ ማዕዘናተ ዓለም በአራቱ ነፋሳት በአርባዕቱ እንስሳት መመሰልና እያንዳንዱን ወንጌላዊ ከአርባዕቱ እንስስ በአንዱ መጥራት የጀመረ አባት ነው:: (P ,205)

ከብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመቀጠል በቤተ ክርስቲያን ቀኖና የገቡት መጻሕፍት በመቀጠል በቤተ ክርስቲያን ቀኖና የገቡት መጻሕፍት ሊቃውንት /ለመናፍ ቃን መልስ ለመስጠትና እውነተኛዋን እምነት ለመመ ስከር የተጻፉ/ ናቸው:: እነዚህ መጻሕፍት መጀመሪያ የተጻፉት በክታብ /ደብዳቤ መልእክት/ መልክ ሲሆን በልዩ ልዩ ቦታ የነበሩ አበው ሊቃውንት አስፈላጊ ወደ ሆነው ቦታ የጻፏቸው ናቸው:: ለዚህም ምሳሌ የሚ ሆኑን አግናጥዩስ ምጥው ለአንበሳ ለደቀ መዛሙርቱ የጻፋቸው አባጅሮም ለሄሊ ቪዲየስ /ቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግል አይደለችም ብሎ መጀመርያ የተነሣ መናፍቅ መልስ የሰጠው በሃይማኖት አበው መጽሐፍ የምናገኛቸው የልዩ ልዩ አበው ጽሑፎች ናቸው::

እነዚህን ጸሕፍት ከቤተ ክርስቲያን መሠረታም እምነት ጋር እያስተያዩ መሠረታም እምነት ጋር እያስተያዩ በዚያ ዘመን የነበሩ አበው በጉባኤ ተቀብለዋቸዋል:: በአንድነት ጠርዘውም የቅሱሳት መጻሕፍ ትና ሌሎችም በቤተክርስቲያን ቀኖና ገቡ::

ከላይ ከተገለጠው ታሪክ መረዳት እደምንችለው ጳጳሳት መጻሕፍትን የመለየት የመወ ሰንና በቀኖና የመቀበል ሥልጣኑ የአሳታ ሚዎች ወይም የምሁራን /Scholars/ ሳይሆን የቤተክርስ ቲያን ነው ቤተክርስቲያን በቀኖናዋ የመጻሕፍትን ቁጥርና ይዘት መወሰንዋ ለክርስቲያኖች ኑሮ ቢያንስ ሶስት ጥቅሞች አስገኝቷል::

1. ጥበቃ:- ቤተ ክርስቲ ያን የቅድሳት መጻሕ ፍትን ቁጥር ወስና ባትጠብቅ ኑሮ በየዘመናቱ እንደ ተነሡት መናፍቃን ብዛት ልዩ ልዩ የኑፋቄ ትምህርቶች ያለ ሐሳብ በተሠገሠጉ ነበር::
2. ውርስ:- ቤተ ክርስ ቲያንን ሲያጠፉ የተነሡ መናፍቃንና አላውያን የመጀመ ሪያ ዓላማቸው ቅዱሳት መጻሕፍ ትን መቆነጻጸልና ማጥፌት ነበር:: ነገር ግን ቤተክርስቲያን በዋሻና በፍርክታ ብሎም በልጆቿ ልቡና አሳድራ በማቆየትዋ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላ ለፉ በቅተዋል::
3. ማረጋገጥ:- ከሁለተኛው መ/ክ/ዘ እስከ ስድስተኛው መ/ክ/ዘመን የተነሡ ግኖስቲኮች እውነተኞቹን መጻሕፍት ከሐሰተ ኞች ጋር ለመቀላቀልና ለማም ጣት ብዙ ጥረዋል:: በሐዋርያት ስም የራሳቸውን ድርሰት አቅርበዋል:: የቶማስ ወንጌል የእውነት ምስክር /የአዳምና ሔዋን ታሪክ/ የጴጥሮስ ራእይ የማርያም ወንጌል /ማርያም መቅደላዊት/እና የመሳሰሉትን በግኖስቲኮች የኑፋቄ ትምህርት የተሞሉ መጻሕፍትን ከእውነተኛው መሠረተ እምነት ጋር በማስ ተያየት ሐሰተኝነታቸውን ያረጋገጠች ቤተክርስቲያን ናት::

ስለሆነም የአዋልድ መጻሕ ፍት የሃይማኖት መጻ ሕፍትነት የሚረጋገጠው በቤተ ክርስቲያን ቀኖና የቅዱሳት መጻሕፍት ማዕረግ ሲሰጣቸው በመሆኑ ቤተክር ስቲያን የተቀበለቻቸውን እን ቀበላለን::

**ቅዱሳት መጻሕፍትን በቀኖና የመቀበል ሥርዓት ሁለት ዓይነት ነው::**

1. ይፋዊ ቀኖና (Offic ial canonicity )
2. ትውፊታዊ ቀኖና (Tradi tional canonicity )

1. ይፋዊ ቀኖና በቤተ ክርስቲያን ሲናዶስ ወይም ሲኖዶስ ባቋቋመው አካል መጻሕፍትን መርምሮ በይፋ የመቀበል ሥርዓት ነው:: ለዚህ አብነት የሚሆኑን የቅዱሳት መጻሕፍትን ማንነት የለዩት /የኒቂያ 325 ዓ.ም / የሬጊዩስ /393 ዓ.ም/ እየንርቴጅ /397ዓ.ም/ ሲኖዶሶች ናቸው:: በእነዚህ ጉባኤያት የአሥራው መጻሕፍት ቁጥር እና ማንነት ተወስኖ በይፋ ተገልጧል:: ከዚህ በተጨማሪ የምእመናን መሪዎች የሆኑ ሐዋርያውያን አበውና ቅዱሳን ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ ትምህርተ ሃይማኖትን እንድታስተምርባቸው ሥርዓት አምልኩትን እንድ ትፈድምባቸው ስለታዘዙት የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር በማስመልከት በገሃድ ያስተላልፏቸው መልእክቶች ይፋዊ ቀኖናት ናቸው::

ለምሣሌ የሊዮን ሊቀ ጳጳስ ሄሬኔዎስ /2ኛው መ/ክ/ዘ በጊዜው ያገኛቸው መጻሕፍት /የብሉያት መጻሕፍትን አርባዕቱ ወንጌልን የሐዋርያት ሥራን 13ቱ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታትን 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ እና 2ኛ የዩሐንስ

መልእክታትን ራእየ ዩሐንስን አሥራውነታቸውን አውጇል:: የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አትናቴዎስም በ367 ዓ.ም በተከበረው የትንሣኤ በዓል ላይ ባስተ ላለፈው ቃለበረከት 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን አሥራውነት አውጇል::

**2. ትውፊታዊ ቀኖና:- /Traditional Canonicity/**

የቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በይፋሳይ ሰበብ በየዘመናቱ የነበሩ ቅዱሳን ከመሠረተ እምነት ጋር እያስተያዩ የተቀበሏቸው ሌሎ ችም ይቀበሏቸው ዘንድ ያስተምሯቸው ትምህርቶች አንድም መጻሕፍት ናቸው:: በጉሊና ሲዘከሩ በአንደበት ሲነገሩ ኖረው በኃላ ዘመን በጽሑፍ የተሰበሰቡት የብሉያትና የሐዲ ሳት አንድምታ ትርጓሜዎች ለትውፊታዊ ቀኖና ቀዳሚት አብነት ናቸው::

ከዚህ በኃላም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተገኙ መጻሕፍት በተጉት ዘመን በነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አማካኝነት ተቀባ ይነት እያገኙ በትውፊታዊ ቀኖና ተወዝግበ ዋል:: በይፋዊም ቀኖና ሆነ በትውፊታዊ ቀኖና ቅሱሳት መጻሕፍቱ በቀኖና ገብተው እስከ ተገኙ ድረስ የሃይማኖት ማጻሕፍት ቅዱሳት መጻሕፍት ተብለው የመጠራት ሥልጣን አላቸው:: ባለፈው እትማችን በመጠኑ ለመግለጥ እንደሞከርነው አዋልድ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅድስ /የአሥራው መጻሕፍት /ልጆች እንደ መሆናቸው በነገር ሃይማኖት በክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሕይወት እና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተጠያቂዎች ናቸው በማስረጃነት በአረነት ይጠቀሳሉ::

ይህ የአዋልድ መጻሕፍት አስረጅነት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ /አሥራው መጻሕፍት / አስረጅነት (Authenticity) ያለ ነው:: በቤተክርስቲያን ሕይወት ያለፉ አበው አዋልድ መጻሕ ፍትን ለነገረ ሃይማኖት ማስተ ማርያ ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ለክርስቲ ያናዊ ሕይ ወት መመሪያ ይሆኑ ዘንድ በማረጋገጫነት እንደጠ ቀሙ የደረጓቸውን መሠረታዊ ምክንያ ቶች ከዚህ ቀጥለን እንመልከት::

**ሀ. በጸሐፊዎቻቸው /Authors Authenticity /**

አዋልድ መጻሕፍትን አጻፋት አበው በመንፈስ ቅድስ የተመሩ በመንፈሳዊ ሕይወት የተጉ ራሳቸውንም ለእግዚ አብሔር ሕግ ያስገዙ ናቸው:: ከምድራዊ ኑሮ አንዳች ጥቅም ለማግኘት ሲሉ መጻሕፍቱን አለጻፏቸውም:: ለሃይማኖታቸው በነበራቸው ቅንዐት የእግዚ አብሔር ቸርነት እንድገለይ የሰው ልቡና በእምነት እንዲቀና የዲያብሎስ ውርደቱ የኃጢአት ክፋቱ ይታወቅ ዘንድ እንጂ ::

በመሆኑም ነው የአዋልድ መጻሕፍት ደራስያን በመንፈስ ቅዱስ ቃኝነት ጽፈዋል የምንለው:: አንዳንድ ሰዎች የመጻሕፍቱ ደራስያን ራሳቸውን ባለመግለጣቸው የመጻሕፍቱን እውነተኛነት ማረጋገጥ አንችልም የሚል ሐሳብ አላቸው:: ነገር ግን ይህ አጻጻፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ጋር ያመሳስላቸዋል እንጂ የሠሩትን ሥራ ክስርና ይቅም አየሳንሰውም:: ለምሳሌ የአርባዕቱን ወንጌል ጸሐፍት ለይተው ወንጌል ዘማነምስ ዘማርቆስ ዘሉቃ ዘዩሐንስ ያሉት የኃላ ሊቃውንት ናቸው:: /የመንጌል አንድምታ ትርኒሜ የማነምስ ወንጌልን ታሪክ ይመለከታል::ከብሉያት መጻሕት የሙሴ መሆናቸውን የመሰከሩት የአሪት መጻሕፍት የሙሴ መሆናቸውን የመሰከሩት የኦሪት ሊቃውንት ናቸው እንጂ ሙሴ እኔ ጻፍኩት አላለም:: ጥህም ከጸሐፍቱ ይልቅ ያስጻፈው እግዚአብሔር ከእንርሱ ማንነት ይልቅ የመጽሐፉ ትምህርት ይገለጥ ዘንድ ስለ ትፀትና የፈጸሙት ነው:: አንድም በእስራኤል ዘንድ ራስን በሶስተኛ ወገን አርቆ መናገርና መጻፍ ልማድ ስለሆነ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ለጢሞ ቴዎስ «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተ ዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሐር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» እንዳለው/2ጢሞ 3-16/:: ቅዱሳት መጻሕፍትም የተጻፋበት ዋና ዋና ዓላማዎች ትምህርት ተግሣጽ ልብን ማቅናትና ምክር ናቸው::

ለምሳሌ አባ ጊዩርጊስ ዘጋ ሥጫ /1358-1417 ዓ.ም/ ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘውን መጽሐፍ የጻፈበትን ምክንያት በመጽሐፍ የጻፈበትን ምክንያት በመጽሐፍ መቅድም ሲገለጥ:-

«ወበአሐቲ ወዋዕል ተስእሎ ለመስፍን ዘስሙ ቴዎድሮስ ዘይሰመይ ካልዕ ሊቀ ሐራ በእንተ ሃይማኖት:: ወሶበ ርዕይዋ ወአንበብዋ ለውእቱ መጽሐፍ ንጉሠ ወኲሎሙ ናህናት ምሥዚር ይብሉ አማን ዩሐንስ አፈወርቅ ወቄርሎስ ተረክቡ በብሔርን::» «ከዕለታት በአንድ ቀን ቴዎድሮስ የተባለ የሠራዊት አለቃ መኰንን አባ ጊዩርጊስን ስለነገረ ርትዕት ጠየቀው አባ ጊዩርጊስም ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘውን መጽሐፍት ደረሰለት ንጉሡ እ ካህናቱም መጽሐፋን ባዩና ባነበቡ ጊዜ ምእውነት ዩሐንስ አፈወርቅን ቄርሎስ በዘመናችን ተገኙ ብለው ተናገሩ::»

እንግዲህ አባ ጊዩርጊስ መጽሐፋን የጻፈው ስለ ሃይማኖቱ በሚገባ በመመስከርና እውነቱ ይገለይ ዘንድ እንጂ የሚያገኘ ው አንዳች ምድራዊ ጥቅም ስለ ነበረ አይደለም:: ሃይማኖትን መመስከርና መግለይ ደግሞ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው:: «በሰው ፊት ለማመስክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለሙ አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ:: እንዳለ ጌታችን በመንጌል» ማቴ 10-32

አባ ኤፍሬም ሶርያዊም ውዳሴ ማርያምን እንዴት እንደ ደረሰ በመቅድሙ ሲገለይ «እመቤታችንንን ከመውደዱ አተነሣ የእመቤቴ ማርያም ምስጋናዋ እንደ ሰማይ ኰከብ እንደ ባሕር አሸዋ በዝቶልኝ እንደ ልብስ ለብሼው እንደ ምግብ ተመግቤው እያለ ሲመኝ ይኖር ነበር:: የፈለጉትን መግለጽ ለእግዚአብሔር ልማዱ ነውና 14.000 ድርሰት ደርሷል» ይላል:: የአባ ኤፍሬም የድርሰቱ መነሻ ለእመቤታችን ያለው ፍቅር ነው::

ገድለ ቅዱሳንንም የጻፋት አባቶች ተመሳሳይ ዓላማና ሕይወት ነው የነበራቸው:: ወንጌ ላዊው ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ሲጽፍ የሐዋርያትን ዱካ ተከትሎ ያየውንና የሰማውን እንደ ጻፈው ሁሉ ያዩትንና የሰሙትን የቅዱሳት ኑሮ የጻፉ አሉ:: ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን የማርያም ግብጻዊትን ገድል የጻፈው ዘሲማስ ዐቢይ ጾምን ለመጾም ወደ ዩርዳኖስ በረሃ በወረደ ጊዜ የጽናናበትን ነገር ያሳየው ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነው:: በበረሃውም ውስይ ይህችን ቅድስት እናት በሩቁ ዐየ:: እርስዋም ታሪኳንና ገድሏን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ነገረ ችው:: እርሱም በቀጣዩ ህመት ሥጋ ወደሙን አምጥቶ ካቆረባት በኃላ ገድኒን ጽፎላታል::

የሚያውቁትን መናገር የሰሙትን መመስከር ይገባል:: ዩሐ3-11:: ይህም አባት ስለዚህች ቅድስት እናት የሚያውቀውን መናገሩ ያየውን መመስከሩ መጽሐፋዊ ግደታውን ተወጣ ተብሎ ያስመሰግነዋል:: ሐዋር ያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ከቀድሞ ጀምሮ የተነሡ ቅዱሳንን እምነ ትና ገድል ነሃይማኖት ምስክር ይሆኑ ዘንድ ዘርዝሯ ቸዋል:: «ጊዜ

ባያጥርበት» ኖሮ ስለ ብዙ ቅዱሳን ይተርክ እንደ ነበር ገልጧል::/ዕብ 11-32/:: በኃላ ዘመን የተነሡ አበውም የነዚህን ቅዱሳት አሠሪ ፍኖታ ቸውን የተከተሉትን የተፈቀደ ላዋሙን ያህል ገድል ትሩፍታቸውን ጽፈውልናል::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ መለኮትን እንድታስ ተምርባቸው ለሥርዓተ አምል ኮትን እንድትፈጽምባቸው ለሥርዓተ ቅዳሴ እንድትገለገል ባቸው የተደነገጉት አምላካው ያት መጻሕፍት ቁጥር 81 ናቸው:: ከእነዚህም መካከል 46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሲኾኑ 35ቱ ደግሞ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው:: ሁሉም ተጠቃለው ቅዱሳት መጻሕፍት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ:: «አምላካውያት» የሚለው የባሕርይ ቅጽል የተሰጣቸው «አምላክ አዝዞ ያጻፋ ቸው የአምላክን ነገር የሚናገሩ» መጻሕፍት በመሆ ናቸው ነው:: /ፍት.ነገሥት አንቀጽ 2 ረስጠአ 81 ረስጠጅ 56/:: ሠላሳ አምስቱ ~~የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከይዘታቸው የኄያ የወንጌል የታሪክ የመልእክት /የትምህርት/ የትንቢትና የሥርዓት መጻሕፍት~~ ተብለው በአምስት ይከፈላሉ ::

ከእኒህም ውስጥ የሥር ዓት መጻሕፍት የሚባ ሉት 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ወደ 35 የሚደር ሱት ስምንቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት ናቸው:: አጠቃላይ መጠሪያቸው ሐዋ ርያውያት ትእዛዛት ዘሰመ ንቱ መጻሕፍት ዘበአደ ቀሌምንጦስ /ስምንቱ መጻሕፍተ ኪዳን /ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀሌም ንጦስ/ ሲሆን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን «ሲኖዶስ ዘቅዱሳት አበዊነ ሐዋርያነት» ወይም በአጭሩ «ሲኖዶስ» (Senodos) የሚለው ኃይለ ቃል የግሪክ /ጽርእ/ ቃል ነው ትርጉሙም ስለ ነገራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባኤ ማለት ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የቤተ ክርስቲያን ቀኖናትና መሰል ሥራዎች ተሰብስበው የሚገኙበትም መዝገብ «ሲኖዶስ» ይባላል «ጉባኤ ቀኖናት ወሥር ዓታት» ወይም «መድበለ ቀኖናት ወሥርዓታት» ማለት ነው:: በዚህ አገባቡ ሲኖዶስ ቀኖና ከሚለው ኃይለ ቃል ጋር ተመሳሳይ ኾኖ ይገኛል በተለያዩ ርእሶች ተቀርጸውና በአንጻራ ቸውም በተለያዩ አንዞች ተመድበው የሚገኙ ቀኖናትን ይይዛልና:: ክፍለ ቀኖናት ወይም ሥርዓታት እያንዳንዳቸውም ሲኖዶስ ይባላሉ:: ስለዚህም ሲኖዶስ በሚለው ሰነድና ስያሜ የሚታወቁት ስምንቱ መጻሕ ፍት ኪዳን የቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው:: የሠሯቸውና የደነገጓቸውም ቅዱሳትን ሐዋር ያትን ሲሆኑ በእነርሱ ትምህ ርትና ትእዛዝት ላይ ተመሥ ርተው በጽሑፍ የቀረጿቸውና ያቀነባበሯቸው ደግሞ ከአንደ በታቸው የተማሩ በእጃቸው የተሾሙ በእግራቸው የተተኩ ሐዋርያዊያን አበው ናቸው:: /ኰኩሐ ሃይማኖት ገጽ 113/:: የቅንብራቸው መነሻ ጊዜ (Terminus a Quo) የሁለተኛው ምዕተዓመት አጋማሽ ሲሆን መፈጸሚያው (Terminus ed Qucm) ደግሞ የሶስተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ነው::

ቅዱሳን ሐዋርያት በተሰበሰቡ ጊዜ ሁሉ ስለ ነገረ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ስለ ናህናት አገልግሎት ስለ ምእመናን ድርሻ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውሳኔዎችን አስቀምጠዋል:: ለስምንቱ መጻሕፍተ ኪዳን ቅንብር መሠረት የኾኑት የቅዱሳን ሐዋርያት ውሳኔዎች 85ቱ ሐዋርያውያት ቀኖናት ይባላሉ:: የውሳኔዎቹ ይዘትና ተፈጻሚነት በዘመነ ሐዋርያት በነበረው የቤተክ ርስቲያን አገልግሎትና አስተዳደር ሁኔታ የተመሠረቱና በዚያም ክልል ብቻ የተገቱ ሳይሆኑ በኋለኛ ው ዘመን ለሚመጣውም የበተ ክርስቲያን አገልግሎትና አስተ ዳደር መርሕ ይሆኑ ዘንድ የተደነገጉ ናቸው:: /መጽሐፈ ትምህርት ዘታዴዎስ መግቢያ ክፍል ተ/:: እነዚህ «እነርሱና መንፈስ ቅዱስ »በአንድ ላይ ኾነው የሠሯቸው ቀኖናት በአንደተታቸው በተማረው በእጃቸው በተሾመው በእግራ ቸው በተተካው በቅዱስ ቀሌምንጦስ አማካኝነት ለኤጲስ ቆጶሳት ለካህናትና ለምእመናት ሁሉ ተልከዋል:: በሌላ በኩል በ85 ሐዋርያዊያን ቀኖናት ከተካተቱት ውስኔዎች የመጨ ረሻው 85ኛ ቀኖና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድ ትቀበላቸው የታዘዙትን ክቡራት ቅዱሳትና አምላካዊያት መጻሕፍት ዝርዝር አመልክቷል በዚህ ቀኖት ዝርዝ ራቸው ከተመለከቱት ክቡራት ቅዱሳትና አምላካ ውያት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መንከለ ስምንቱ መጻሕፍተ ኪዳን ይገኙበ ታል::«ሐዋርአውያት ትእዛዛት ለእናንተ ኤጲስ ቆጶሳትና ናህናት በኔ በቀሌምጦስ እጅ ተላኩ:: ለሁላችሁም ካህናትና ምእምናን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕ ፍት ቅዱሳትና ክቡራት ይሁኑ::» /85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ፍትሐ ነገሥት መቅድም ገጽ 13/::

ቅዱስ ቀሌምን ጦስ በ90 ዓ.ም ገደማ የሮሜ መንግሥት ዋና ከተማ በነበረችው የሮማ መንበር ጳጳስ የሆነ የሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ረድአ ነበር:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጱስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «በሕይወት መጽሐ ፍ ከተጻፋት ከቀሌምንጦስ እና ደግሞ ከእኔ ጋር አብረው ከሠሩት ከሌሎቹ ጋር በወንጌል ከእኔ ጋር አብረው ተጋድ ለዋልና» ያለው እርሱን ነው:: /ፊልጵ 4-3/ (EERDMANS DICTONARY OF THE BIBLE P.263) ቅዱሳን ሐዋርያት የሊቀ ሐዋርያቱ ቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር በሆነው በቀሌምንየስ እጂ መላካቸው የ8ቱን የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕት አሥራውነትና ሥልጣን የሚያረጋግጥ (Certificate of canonicity and Authenticity) ነው:: ስለ ክብራቸውና ቅድስናቸው ከቅዱሳት ሐዋር ያት የሚያውቀውን ሲናገር የሰማውን ሊመሰክር ይችላ ልና::ምስክርንቱም እርግጥ ነው:: /ሐመር 10ኛ ዓመት ቁ 1:ገጽ 11/

## ስምንቱ መጻሕፍተ ኪዳን የተጻፍበት ቋንቋና ትርጉሞች

ስምንቱ መጻሕፍተ ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፋበት እናት ቋንቋ ሱርስጥ /የሶርያ ቋንቋ/ ነው:: አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ~~በኃለኛው ዘመን እኒህን የሕግና የሥርዓት መጻሕት በየቋንቋው ለመተርጎም መነሻ ሆነው የገለገሉት ሰነዶች በሙሉም ሆነ~~ በከፊል ተቀርጸው የተገኙት በግሪኩ ቋንቋ ስለሆነ ስምንቱ መጻሕፍት ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፋት በርራክ ልሳነ ጽርእ ይላሉ ሱርስጡንና ርሪኩንም ነው:: መሠረት በማድረግ ወደ ላቲን /ሮማይ ስጥ/ ግብጥ /ሳዲቅ እ ሜምፊቲቅ/ ዐረብኛ ግእዝ ቋንቋዎች በተለያዩ ወገኖች /ንስጥሮሳውያን መለንውያን ያዕቆባውያን ሶርያውያን በተለያዩ ሥፍራዎች /ሶርያ ግብጽ/ እና ጊዜያት ተተርጉመዋል:: ፍትሐ ነገሥት መቅድም/ በተጨማሪም በጀርመንኛ በፈረንሳይኛ በእንግሊዝኛና መሰል ቋንቋዎች ተተርጉመዋል:: በሀረንችን መጻሕፍቱ ወደ ግእዝ ቋንቋ የተተረጎሙት ከዐረብኛው ሰነድ ነው:: እንደ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ የሊቃውንት ጉባኤ አባል ደግሞ ለግእዙ ትርጉም ጥንቱ የሱርስጡ ሰነድ ነው:: ይዘቱም ከቅብጥ ትርጉም ሰነድ የበለጠ ምልዓትን ያሳያል በተጠቀሱት ቋንቋዎ ትርረም ሂደት የይዘት መጨመር መቀነስ መለዋወጥ መዘዋወር በከፍተኛ ደረጃ ይታይባቸዋልና::

## የስምንቱ መጻሕፍት ኪዳን ዝርዝርና ይዘት

### 1.መጻሕፍተ ኪዳን

1.1 መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 59 አንቀጽ ያለው የጸሎትና የሕግ መጽሐፍ ነው:: በዚ አገባቡ«ኪዳን» የሚለው ቃል ትርጉም ትምህርት ምስጋና ማለት ነው:: ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኃላ ከዕርገቱም በፊት ለአሥራ አንዱ ቅዱሳት ሐዋርያት በገሊላ ለ40 ቀናት እየተገለጠ ያስተማራቸው እየጠ የቁት የመለሰላዋው የሥርዓት ቤተ ክርስቲያን

ትምህርት ነው:: «ኪዳን ዘነገሮሙ እግዚእን ለአሠርቱ ወአሐዱ አርዳኢሁ» እንዲል:: /መጽ ኪዳቀዳ ክፍል 1 ግቢ.ሐዋ 1-2-3/ ሊቃወንተ ቤተ ክርስቲያንም ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ሳለ ያስተማረው ትምህርት ወንጌል ይባላል ከሞቱና ከትንሣኤው በኃላ ያስተማረው ግን «ኪዳን»(Testament of the Lord ) ይባላል ብለው ያትታሉ::, በዚሁ መጽሐፈ «ኪዳን» መጨረሻ የጸሐፊዎቹ የቅዱሳት ሐዋርያት ስም ተዘርዝሯል:: «ዩሐንስ ወማቴዎስ ወቶማስ ወጴጥሮስ እዱርያስ ወበርቶሎሜዎስ ያዕቆብ ወፊልጶስ ወናትናኤል ወይሁዳ ወያዕቆብ ጸሐፍነ ለቤተ ክርስቲያን ዘጽባሕ ወዐረብ ለእለ ደቡብ ወሰሜን»::

የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ይዘት ሥርዓተ ጸሎትና ሥርዓተ ቅደሴ ነው:: ለምሳሌ ጸሎተ ኪዳን ዘእግዚኦ እንዲ ጸለዩባቸው በተመደቡ ሶስት ጊዜያት /ጸሎተ ኪዳን ዘሠለስቱ ጊዜያት/ ተከፍለው የሚገኙ ኪዳናትን/ ይዟል:: እኒህም:-

1. ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት
1.1 ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኵሉ
1.2 አምላከ ብርሃን ወላዴ ሕይወት
1.3 ንሜልስ ለከ ዘንተ ስብሐተ ኪዳን ዘነግህ
2. ኪዳን ዘነግህ
2.1 እዚአብሔር አብ ወሃቤ ብርሃን
2.2 እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዓነ ቅዱስ
2.3 ንሜልስ ለከ ቅዱስ ስብሐት
3. ኪዳን ዘሠርክ
3.1 ለከ ለአብ ዘኢይማስን መድኃኔ ነፍስነ
3.2 ለዊድስከ እዚኦ
3.3 ለከ ዘእም ልብነ ናቸው:: /መጽሐፈ ሲኖዶስ መጽሐፈ ቅዳሴ ግእዝና አማርኛ ገጽ195-197/::

ጸሎተ ኪዳን ዘእግዚኦ ከሰሙነ ሕማማት በቀር ዘወትር ጧት ጧት ላይ ጸልዩ አዋው ሉም:: የማደርሱትም በዜማና በንባብ ነው፡ በሰሙነ ሕማማትም ቢሆን ከሰሆና እከ ዓርብ በአንድምታ ትርጓሜ ይደረሳሉ:: ሌላው ትምህርተ ኅቡአት ሲሆን በጊዜ ቅዳሴ ከእግዚኦታ በኃላ ይነበባል:: በስብከት በኖላዊና በጥምቀት በመልክ ኢየሱስ ፈንታ በዜማ ይደረሳል:: በሰሙነ ሕማማትም ለምእመናን በአንድ ምታ እየተተረጎመ ከኪዳን ጋር ትምህርት ይሰጥበታል:: እዚአብ ሔር አብ ዘብርሃናት በእተ ቅድሳት በሰማይ የሀሉ ልብክሙ ቅዳሴ እግዚኦ እና ፍትሐት ዘወልድም ከመጽሐፈ ኪዳን ቀዳመዊ የተውጣጡ የሥርዓተ ቅዳሴ ክፍሎች ናቸው::/የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት 5 ገጽ 31-35/::

1.2 መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ:-

ሁለተኛው መጽሐፈ ኩዳን በስድ ንባብ መልክ የተቀረጸ ነውቸቸ አጠቃላይ ይዘቱ ስለ ዳግም ምጽአት ስለ ሐሳዊ መሲሕ ስለ ናህናት ከፍተኛና ዝቅተኛ ሹመትና አገልግሎት ስለ ምእመናትና ንዑሳነ ክርስቲያን ሥርዓተ ጥምቀትና ምሥጢረ ቁርባን የሚናገር ነው::

2. አራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስ:-

2.1 ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ:-

ይህ የቀኖና መጽሐፍ ቅዱሳን ሐዋርያት ከዕርገተ ክርስቶስና ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ከወረደ በኃላ ለስብከተ ወንጌል ከመበተናቸው አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን ተሰብሰበው ሳሉ የሠሩት የቀኖና መጻሕፍት መጀመሪያቸው /ለመጻሕፍተ ቀኖናትሰ ቀዳሚ ሆሙ መጽሐፈ ቀኖናት ዘሠር ዕዎን ሐዋርያት (Apostolic Canons)ነው:: የቀኖናቱ ቁጥር 30 ሲሆን መሪ ምልክታቸው ትእምርተ ጥቅሳቸው በምኅጻረ ቃል «ዓይን» ይባላል:: የምኅጻረ ቃሉ አመጣጥም የመጀመሪያወ ፊደል «ዓ» ከጽርሐ እና «ይን» ከጽዮን ሁለት ቃላት ተወስዶ ከጽርሐ ጽዮን ሥርዓተ ጽዮን «ዓይን» እንደተወለደ ይነገራል:: በሌላ በኩል «ዓይን» ሐዋርያት ከተሰበሰቡበት የጽርሐ ጽዮን ሰገነት የመጀመሪያው ፊደል ነው ይባላል:: የመጽሐፈ ሲኖዶስ የመጀመሪያው ክፍል የኾነው ሥርዓተ ጽዮን «ሲኖዶስ ቀኖናት ዘጽዮን » ወይም «መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት» ተብሎም ይጠራል:: ከይዘቱም ለምሳሌ ስለ ሶስቱ መዓርጋተ ክህነት አገልግሎትና ሥነ ምግባር ስለ በዓለ ልደት ስለ በዓለ ጥምቀትና ስለ በዓለ ዕርገት አከባበር ስለ ሰማዕታት መታሰቢያ ቅድመ ቁርባን በእሑድ በረቡዕ በዓርብና በዘወትር ቀናት ስለሚደረጉ ጸሎቃት ፊትን ወደ ምሥራቅ አዙሮ ስለ መጸለይ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ ወዘተ የተሠሩት ድንጋጌዎችና ትእዛዛት ይገኙበታል:: እንዚህም ትእዛዛት ተፈጻሚነት በዘመነ ሐዋርያት በነበሩት ሁኔታዎች ላይ የተመሠረቱ ብቻ ሳይሆኑ ከእነርሱም በኃላ ለሚመጣው ዘመን የተደነገጉ ናቸው :: /መጽሐፈ ትምህርት ዘታዴዎስ መግቢያ ክፍል ተ/ በመሠረሻም ቅዱሳት ሐዋርያትና አርድእት ለስብከተ ወንጌል ተከፋፍለው የተሠማሩባቸውን ቦታዎች በቁጥር ይዘረዝራል::

2.2 አብጥሊስ ሲኖዶስ:- 82/83 ቀኖና /አንቀጽ/ ያለበት የመጽሐፈ ሲኖዶስ ክፍል ነው:: አብ/ጠሊስ-አፖስቶሎስ አፖስቶሊ ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ተጥላሳት ከሚለው የሀረብኛ ቃል ጋር አንድ መሆኑ ተመልክቷል:: በመጽሐፈ ሲኖዶስ እንደተ ጠቀሰው ትርጉሙ ሐዋርያውያት ቀኖናት ማለት ነው «ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጥ ሊሶሙ» እንዲል:: /መጽሐፈ ቅዳሴ ግእዝና አማርኛ ምዕ3 ሚመጠን ግርምት ቁ3 ገጽ 12/:: በመጽሐፈ ሲኖዶስ አብጥሊስ የሚነሣበት ርእስ «ሲኖዶስ ቀኖናት በሐዋርያት ቅዱሳን ዘዘነወ ቀሊምንጦስ በእንተ ጴጥሮስ የጸፉትና አብጠሊሳት ተብላ የምትጠራውና ቁጥራቾ ውም 82 የሆነ» የሚል ነው::

የመጀመሪያው ቀኖና /አብጠሊስ 1/ በመጥሮጳሊስ የተጠሩ ምእመናነ ክርስቶስ በተገኙበት ኤጲስ ቆጶስ በሰንበተ ክርስቲያን በሶት ክልቻለ በሁለት ኤጲስ ቆጳሳት እንደሚሠየም ሲደነገግ 82ኛው ቀኖና ደግሞ «ምእመናን እንዚህን መጻሕት ይጠብቁ:: በክርስቶስ ስም ለምእመናን ያዘዝናቸው የቤተ ክርስቲያን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስሞች የሚከተሉት ናቸው:: እዚህም መጻሕፍት ከእግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅድስ የወረቡ መጻሕፍት ዜና ሲሆኑ እንርሱም ትእዛዝ ይባላሉ ቁጥራቸውም 81 መጻሕፍት ናቸው::» ይላል በተጨማሪም ስለ ካህናት አገልግሎትና ሥነ ምግባር ስለ ምእመናን ተግባራት ሥነ ምግባ ርና ግደታዎች ስለ ምሥጢረ ቁርባን ስለ ካህናት ጋብቻ ስለ ዐርባ ጾም እንዲሁም ስለ መጻ ሕፍተ ሐሰት ወዘተ የሚወስኑና የሚከለክሉ ቀኖናት አሉት::

የአብጥሊስ ሲኖዶስ መሪ ምልክቱ ትእምርት ጥቅሱ «ረስጠአ» የሚለው ምኅጻረ ቃል ነው::

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት «ረስ» ሩሱል /RUSEL/ ከሚለው ዐረብኛ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ሐዋርያት ማለት ነው:: ሶትተኛው ፊደል «ጠ» ቀኖናቱ ወደ ምእመናን ሁሉ ከተላኩበት ረዱእ ቀሌም ንጦስ ከሚለው ስም በማሳጠር የመጣ ነው:: አንድም ተጥላሳት የሚለው የዐረብኛ ቃል በማሳጠር የተወሰደ ሲሆን «ቀኖናት-ትእዛዘት» ማለት መሆኑ ተመል

ክቷል:: «አ» በግብጻውያን አኀዝ የአቆጣጠር ሥርዓት አንደኛ ቀዳማዊ ማለት ነው:: «ረስጠአ» ማለትም «ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ » ሲሆን ቅዱሳን ሐዋርያት በረድአ ቀሌምንጦስ አማካኝነት የላኩት የመጀመሪየው የሥርዓት መጽሐፍ ማለት ነው::

2.3 ትእዛዝ ሲኖዶስ:- 71/72 ቀኖና /አንቀጽ/ ያለበት የሲኖዶስ መጽሐፍ ክፍል ነው:: ትእዛዝ የሚለው ስም ቀኖና የሚለው ጋር ተመጣጣኝ ነው:: በመሆ ኑም «ቀኖናት ዘአበው ሐዋርያት (Canons Apostolic) በብሉ ይጠራል:: የትእዛዝ ሲኖዶስ መሪ ምልክቱ ትእምረተ ጥቅሱ በምን ጻረ ቃለ «ረስጠብ» ይባላል:: ስለ «ረስ» እና «ጠ» የሚሰጠው ማብ ራሪያ አስቀድሞ እደተገለጠው ሲሆን የመጨረሻሬ ፊደል «ብ» በግብጻውያን አኀዝ አቆጣጠር ሥርዓት የቀኖነቱን ቅደምተከ ተል የሚጠቁም ሲሆን «ሁለተኛ ዳግማዊ» እደማለት ነው:: ስለዚ ህም«ረስጠብ» ማለት ሐዋርያው ቀኖት ቀሌምንጦስ አማንኝነት የላኩት ሁለተኛ የሥርዓት መጽሐፍ ማለት ነው:: የቀኖናው የመጀመሪያ ክፍል /ትእዛዝ/ «የቤሉ ዩሐንስ..» ብሎ የሐዋር ያትን ስሞች ይዘረዝራል የመጨ ረሻው ቀኖና ትእዛዝ 72 ስለ ሥርሀተ ክህነት ይናረራል:: በተጨማሪም ስለ ዐርባ ጾም ፋሲካን ከአይሁድ ፋሲካ ጋር አብሮ ስለ አለማክበር ስለ ረቡዕና ዐርብ ጾም በዓመት ሁለት ጊዜ የሲኖዶስ መጠራት በኤጴስ ቆጶስ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስለ መጻሕፍተ ሐሰት .... አስመልክቶ የተላለፈ ትእዛዛት ይገኙበታል::

2.4 ግጽው ሲኖዶስ:- 56/57 ቀኖና /አንቀጽ/ ያለበት የመጽሐፈ ሲኖዶስ ክፍል ነው:: ግጽው ማለት የታየ የተገለጠ ግልጥ ጉልሕ ሥዕለ ምስል ባለሟል ማለት ነው:: /ኪ.ወ.ክ ገጽ 329-330/:: በመጽሐፈ ሲኖዶስ የሚጠራበት ርእስ « ሲኖዶስ ዘበተ ክርስቲያን ዘወሀብዋ ሐዋርያት ቅዱሳት በእደ ቀሌምንጦስ»(Canons Ecclesiastic) የሚል ነውው:: የግጽወ ሲኖዶስ መሪ ምልክቱ ትእምርተ ጥቅሱ «ረስጠጅ» ይባላል ስለ «ረስ» «ጠ» የሚሰጠወ ማብራሪያ አስቀድሞ እንደተገለጠው ሲሆን «ጅ» ደግሞ በግብጻዊያን አኀዝ አቆጣጠር ሥርዓት «ሶስተኛ ሣልስ» እንደማለት ነው:: በመሆኑም «ረስጠጅ» ሐዋሪያዊት ቀኖናት ቀሌምንጦስ ሣልስ» ማለትን ያመለክታል:: ይኸውም ቅዱሳን ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ የሰጡት ሶስተኛ መጽሐፍ ማለት ነው:: የግጽው ሲኖዶስ የመጀሪያው ቀኖት /ትእዛዝ/ ለአንድ ኤጲስ ቆጳሳት መገኘት እንደሚኖርባቸው ሲያስረደ የመጨረሻው ቀኖና ደግሞ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህ ርተ መለኮትን ለማስተማር ሥርዓተ አምልኮትን ለመፈደም ልትቀበላቸው የማገቡ የ81ዱን አምላካውያት መጻሕፍት ዝርዝር ይናገራል:: በተጨማሪም የኤጲስ ቆጳሳት ምርጫ ቢያንስ በ12 ሰዎ መከናወንና ስለዚህም የአቅራቡያ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጳሳት መጠራት በችግር ወቀት ኤጲስ ቆጰስ በአንድ ኤጲስ ቆጰስ መሾም ስለ ከከብ ቆጠራዎች ወዘተ የተላለፋ ቀኖናት ይገኙብታል::

አስቀድሞ እንደተገለጠው በተለይም በሶስቱ ማለትም በረስጠአ ረስጠብና ረስጠጅ መካከል የሚታየው የጐላ የይዘት ተመሳሳይነት ለቀኖናቱ ቅንብር የግራ መሠረት ከኾነው 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በመነጨ ነው:: እንዲያውም በረስጠብ ምኀጻረ ቃለ የሚጠሩ 56/57 ቀኖናት ከአንድ መጽሐፍ ወደ ሁለት የተከፈሉ እንደሆነ ይታወናል በፍትሐ ነገሥት መቅድም ይህነኑ በማረጋገጥ «እያንዳንዱ ውስጥ ካለው የሚበልጥ የሚናገሩ ሁለት መጻሕፍት አድርገው አውጣ ጡት::» ይላል ስለ አጠቃላይ ተመሳሳይነታቸውም «በእነዚህም ሶስቱ መጻሕፍት በነገር ይተባበራሉ በአከፋፈል ቁጥር ግን የተለያዩ ናቸው አንዱ በሁለተኛው ላይ ከጥቂት በቀር አይጨምርም» ሲል ያስረ ዳል::/ፍት.ነገ. መቅድም ገጽ 13/ ከአራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስ መካከል ሶስቱ ማለትም ረስጠአ ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ ረስጠብ ቀሌምንጦስ ዳግም እና ረስጠጅ ቀሌምንጦስ ሣልስ በቤተ ክርስ ቲያናችን መድብለ ሕግጋት መጽሐፈ ሕግጋት ዐበይት የሚባ ለው ፍትሐ ነገሥት በጸሐፊው እብነ እል አሳለ(AL-SAFI IBN AL-ASSAL)በተቀነባበረ ጊዜ 22 አንቀጾችን ለያዘው ለፍትሕ ወንፈሳዊ ክፍሉ ሁነኛ ምንጭ ሆነው አገልግለዋል:: /ፍጽሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው ይመልከቱ/ ይኸም ለቀኖና ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ዝግጅት መሠረት መሆናቸውን ያስረዳናል ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን ሥርህት መጻሕት ሐዋርያውያት ቀኖናት (Ecclesiastical canons of the Apostles) ተባሉ::

3. ዲድስቅልያ:- በ43 አንቀጾች የተከፈለ መድበለ ትምህርታት ወተግሣጻት ነው በሌላ አጠራር «ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት» ይባላል ዲድስቅልያ ዲዳስካልያ የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ትምህርት ማለት ነው:: በፍትሐ ነገሥት የሚጠቀስበት ምልክቱ ትእምርተ ጥቅሱ «ድስቅ» የሚለው ምኀጻረ ቃል ነው:: እርሱን ጽፎ ለማኖር 12ቱ ቅዱሳን ሐዋርያትና የተመረጠው ጳውሎስ የኢየሩ ስሌም ኤጲስ ቆጰስ ያዕቆብም በኢየሩሳሌም በ50 ዓ.ም ጉባኤ አድርገዋል:: ይኸውም በግብረ ሐዋርያት ምዕ.15/1-29 ላይ የሚገኘውን ሥርዓት ከወሰኑ በኃላ የተካሄደ ጉባኤ ነው:: ከቀኖናት ምንም የሚያንስበት የለውም ከውስጡም በየአንቀጹ ላይ ከወንጌላትና ከብሉያት መጻሕፍት በተለይም ከመዝሙረ ዳዊት ከመጽሐፈ ምሳሌ ከትንቢተ ኢሳይያስ ከትንቢተ ኤርሚያስና ከትንቢተ ሕዝቅኤል በረካታ ምስክር አደረጉለት በመጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ርሪክ መሆኑ ቢታመንበትም ከተወሰኑ ክፍሎቹ በቀር እናት ሰነድ ጠፍቶ (Codex) በሙሉ መልኩ ይዘቱ በመጀመሪያ ሊገኝ የቻለው በሱርስጥ ትርጉሙ (Didascalia Apostolorum Syriac)በ19ኛው ምእተ ዓመት ነው:: ይህ መጽሐፍ ቀደም ሲል ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉሞና ተጠብቆ ኖሯል:: እንዲያውም ከፍተኛ ዋጋው ቀደምብሎ ስለታ ወቀ ከእንግሊዝኛ ትርጓ ሜው ጋር በአውሮፓ ታትሟል::

ዲስቅልያ በአጠቃላይ ይዘቱ ሥርዓት ቅዳሴን ቀኖናዊ ሥርዓትንና ክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር ትምህርትን ይዞ የሚገኝ ሰነድ ነው:: ለምሳሌ ምክርስ ቲያናዊ ሥነ ምግባር ክፍሉ በቤተሰቦች መካከል መረዳዳትና መከባበር ማለትም ሚስቶች ለባሎቻቸው ባሎሀትም ለባልተቤ ቶቻቸው ታማኞች ሆነው ስለመገኘት /ዲድ ቁ21/ አቅመ ደካሞችንና ችግረኞችን መርዳት እንደሚያስፈልግ ራስን ግን መርዳት ሲቻል ለሌላ ሸክም መሆን እንደማይገባ /ዲ.ድ ቁ.18/ ይቅርባይነትን /ዲ.ድ.ቁ9/ የሚያ መለክቱ ድንጋጌዎችን ይዟል:: በሥርዓተ ቅደሴ ክፍሉም ደያቆና ትና ደያቆናዊያት በአገልግሎት ስለሚጠበቅባቸው ግዴታ ስለ ዘጠኙ የጌታችን ዐቢይት በዓላት /ትስብእት ልደት ጥምቀት ሆሳዕና ትንሣኤ ዕርገት ጰራቅ ሊጦስ ደብረ ታቦር ደብረ ዘይት የየዛቸወ ድንጋጌዎች ጥየቀሳሉ በቀኖናዊ ሥርህት ክፍሉም አንድን ኤጲስ ቆጰስ በቸር ጠባቂ /እረኛ/ እና ሐኪም በመመሰለ ለምእመናን ሊያደ ርግላቸው የሚገባውን መንፈሳዊ ጥበቃና የፍትሕ መንፈሳዊ ተግባር ያመለክታል::

4. መጽሐፈ ቀሌም ንጦስ:- ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውና ቅዱስ ቀሌምንጦስ ከእርሱ አግኝቶ የጻፈው ነው ቀደም ሲል እንደ ገለጠው ቅዱስ ቀሌምንጦስ በመጀመሪያ የቅዱስ ጴጥሮስ ረድአና ደቀመዝሙር የነበረ ሲሆን በ90 ዓ.ም ገደማ የሮም መንበር ጳጳስ ሆኗል ይህ መጽሐፍ በሰባት ክፍል የተከፈለ መጽሐፍ ሲሆን ሶስት መጻሕ ፍቱ እንደ አንድ ተቆጥረዋል:: ምልክቱም «ጴጥ» ነው:: ይኸውም ጴጥሮስ ማለት ነው:: ይዘቱም ሥርዓተ ቅዳሴ ያዊና ቀኖናዊ ቅርጽ ያለው ነው:: ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቅርጹን አስመልክቶ ስለ ጸላተ ኪዳን ቡራኬ ማለትም በኤጲስ ቆጰስ አዲስ ቤተ መቅደስ የሚባረ ክበትን ሥርዓት ሥርዓተ ቁርባን ይናገራል በቀኖናዊ ክፍሉም ስለ ሰማዕታትና ሐዋርያት መታሰቢያ ስለ ክብረ በዓላት ስለ ሰንበት ክርስቲያን የዕረፍት ቀን መሆን በሰሙነ ሕማማት የምእመናን ከተግባረ ሥጋ ማረፍ ግዴታ ስለመሆኑ ያትታል:: ቀኖና1-11/:: በመጨረሻም እኒህ ስምንቱ መጻ ሕፍተ ኪዳን በቤተ ክርስቲያን ስም በተለያዩ ጊዜያት በወጡ የመጽሐፍ ቅዱስ

ጎትመቶች ላይ ያልታዩት በይዘታቸው የቀኖና ቤተ ክርስቲያን /የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት/ መጻሕፍት በመሆናቸው ነው:: ስለዚህም ነገር «እነዚህ ስምንቱ መጻሕፍተ ቀሌምንጦስ በውስጣቸው በያዟ ቸው ምሥጢራት ምክንያት ከካህናት በስተቀር ለምእመናን እንዳየሠራጩ» የሚል የትእዛዝ አብነት ይገኛል:: መጽሐፈ ሴኖዶስ ገጽ 90 ረስጠአ 81 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ስለሆነም በጥያቄው እንደ ተመለከተው በጎትመት ላይ ባለመዋላቸው እንደ መጽሐፍ ለየብቻቸው ለይቶ ለማጥናት አልተቻለም ዙሮ ዙሮ አራቱ መጻሕፍት መሠረት ሆነው በየአንቀጹና በየገጹ በመጠቀሳቸው ሥርዓተ ቅዳሴው ሥርዓተ ምሕላውና ሥርሀተ ጸሎቱም ከመጽሐፈ ኪዳን የተውጣጣ በመሆኑ እነሱን ለማጥሀትና ለማወቅ ያለው ሁኔታ ፈጽሞ የማይቻል መስሎ አይታይም::

«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፉ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» /2ጢሞ 3፡16/ በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረውን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለምክርና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር የሚጠ ቅሙ አያሌ ቅዱሳት መጻሕፍት» ከሌሎቹ በመለየት «ቅዲሳት መጻሕፍት» በማለት የምትጠ ራቸው ሲሆን እንዚህም በሁለት የተከፈሉ ናቸው::

1. አሥራው መጻሕፍት /አምላንውያን መጻሕፍት /ፍ.ኒ አንቀጽ 2/
2. አዋልድ መጻሕፍት

አሥራው /አምላካውያን/ መጻሕፍት:-

እነዚህ መጻሕፍት ለሃይ ማኖት ትምህርት ለሥርዓትና ለሕግ መሠረታውያን ለሌሎች መጻሕፍትም የመጨረሻ ምሥ ክሮተ በመሆናቸው አሥራው /መሠረቶች/ ወይም አምላካውያን የእግዚአብሔር መጻሕፍት ተብ ለዋል:: መሠረት ናቸውና ከነርሱ ሌሎች ተወደዋል:: አምላ ካውያን ናቸውና የእግዚአብሔር መጻሕፍት ተብለዋል:: መሠረት ናቸውና ከነርሱ ሌሎች ተወል ደዋል:: አምላካውያን ናቸውና የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ስለ አምላካቸው ለማወቅ ሕጉንና ትዕዛዙንም ለመማር በግንባር ቀደምነት ይጠቅሷቸዋል:: አዋልድ መጻሕፍት:- አዋልድ ማለት «ልጆች» ማለት ነው አሥራው መጻሕትን የሚተረጉሙ የሚያብራሩ በአሥራው መጻሕፍት የተሰጡ ትምህርቶች በቅዱሳን ሕይወት በተግባር ሲገለጡ የሚያሳዩ ምእመናን አሥራው መጻሕትን መሠረት አድርገው ሊመሩባቸው

የሚገቡ ሕግና ሥርዓ ቶችን የሚያስተምሩ የአሥራውን መስለው አሥራውን አህለው የወጡ በመሆናቸው አዋልድ ተብለዋል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን አንዱን ከሌላው አስተባብራ በአሥራው የረቀቀውን በአዋልድ ገልጣ በአዋልድ የቀረበውን ከአሥራው አገናዝባ የተቀበለች ቤተ ክርስቲያን መሆንዋ ብቻ ሳይሆን በተቀበለቻቸው የአሥራ ው መጻሕፍት ቁጥርም ልዩ ያደርጋታል:: ከሌሎች በተለየና በላቀ መንገድ አሥራው መጻሕ ፍትን አሟልታ ትቀበላለች:: በዚህ የተነሣ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት (Broader common ) ይሉታል:: (The Bible through the Ages. P.13)

ፕሮቴስታንቶች 66 ካቶሊኮች 73 ግሪኮች ደግሞ 76 መጻሕፍት ብቻ ይቀበላሉ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው አርባ ስድስት መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው::

ኦሪት ዘፍጥረት
ኦሪት ዘጸአት
ኦሪት ዘሌዋውያን
ኦሪት ዘኁልቁ
መጽሐፈ እያሱ ወልደ ነዌ
መጽሐፈ መሳፍንት
መጽሐፈ ሩት
/እነዚህ ስምንቱ ብሔረ ኦሪት ይባላሉ/::
መጽሐፈ ዩዲት
1ኛ እና 2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል
1ኛ እና 2ኛ መጽሐፈ ነገሥት
መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ
መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ
ዕዝራ ካልዕ እና ዕዝራና ሱቱኤል
መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
መጽሐፈ መቃብያን ካልዕና ሣልስ
መጽሐፈ አስቴር
መጽሐፈ ኢዮብ
መዝሙረ ዳዊት
መጽሐፈ ምሳሌ
መጽሐፈ ተግሣጽ
መጽሐፈ ጥበብ
መጽሐፈ መክብብ
መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን
ትንቢተ ኢሳይያስ
ትንቢተ ኤርምያስ
ትንቢተ ሕዝቅኤል
ትንቢተ ዳንኤል
12 ደቂቀ ነብያት/ሆሴዕ አሞጽ ኢዩኤል ሚክያስ አብድዩ ሐገ ሶፎንያስ ዕንባቆም ናሆም ዘካርያስ
መጽሐፈ ሲራክ
መጽሐፈ ዩሴፍ ወልደ ኩርዩን

*መጽሐፈ ኩፋሌ*
*መጽሐፈ ሄኖክ/ፍካ ትርጓሜ አንቀጽ 2/*
*ድምር 46*

እነዚህ አሥራው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በቀኖናና በሥልጣን (Authenticity) እኩል ናቸው:: ቅዱሳት መጻሕፍት አምላካውያት ሲባሉም ከነዚህ አንዱም ሳይጐድል ሌላም ሳይ ጨመር ማለት ነው::/ፍካ አንቀጽ 2 ቁ19/

ከነዚህ መጻሕፍት መካ ከል ግን የፕሮቴስታንቱ ዓለም ሙሉ በሙሉ የማይቀበሏቸው ሌሎች እምነቶች ደግሞ ስላላገኙዋቸው አንዳንዱን ብቻ የማቀ በሏቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕ ፍት ይገኛሉ:: የዚህ ጽሑፍ ዋናው ትኩረትም የነዚህን መጻሕፍት አሥራውነት (Canonicity) እና ሥልጣን (Authenticity) ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት አንጻር ማሳየት ይሆናል::

እነዚህ የፕሮቴስታንቱ ዓለም በሙሉ የማይቀበሳቸው አሥራው መጻሕት «ዲዩትሮካ ኖኒካል» በመባል ይታወቃሉ:: ዲዩትሮ ካኖኒካል /በ1980 ዓ.ም በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን የታተመው መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ ስም ነው የሚጠራቸው ማለት ቃሉ የግሪክ ሲሆን «ሁለተኛ የቀኖና መጻሕፍት» ማለት ነው:: እነዚህም መጻሕ ፍት በሁለት ይከፈላሉ::

*ሀ. ራሳቸውን ችለው የማቆጠሩ*

1. ዩዲት
2. *ዕዝራ ካልዕ*
3. እዝራ ሱቱኤል
4. *መቃብያን ቀዳማዊ*
5. *መቃብያን ካልዕ*
6. ጦቢት
7. *ሲራክ*
8. ዩሴፍ ወልደ ኩርዩን
9. ኩፋሌ
10. ሄኖክ
11. ጥበብ ናቸው::

ለ. *ከሌሎች መጻሕፍት ጋር የሚቆጠሩ*

1. *መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ*
2. *ተረፈ ኤርሚያስ*
3. *ተረፈ ዳንኤል*
4. ባሮክ
5. ጸሎት ምናሴ
6. *መጽሐፈ አስቴር*
7. *መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ*
8. *መጽሐፈ ሶስና*

እነዚህ መጻሕፍት ዲዩትሮ ካሮኒካል የተባሉበት ዋናው ምክንያት በቀኖና የተመዘ ገቡበትን የታሪክ ምዕራፍ ለማመልከት ብቻ ነው::

የብሉይ ኪዳን መጻሕ ፍትን የቀኖና ምዕራፍ በሁለት መክፈል ይቻላል::

1. የመጀመሪያዎቹ የብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት / እነዚህን መጻሕፍት በዘመነ ሚጠተ እሥራኤል ካህኑና ጸሐፊው ዕዝራ በሠራው ቤተ መጻሕፍት አስቀምጧቸዋል:: በዚህ ወቅት የተሰባሰቡት መጻሕፍት በአይሁድ እጅ የተገኙት ብቻ ነበሩ በሳምራዊያንና በኤሴያውያን እጅ የነበሩ መጻሕ ፍት በወቅቱ አልተሰበሰቡም:: ከነዚህም መካከል መጽሐፈ ሄኖክና ኩፋሌ ይገኙበታል:: (The Bible Through the Ages p 127)

በ2መቃ 2-3 ነህምያ ቤተ መጻሕፍት ባቋቋመ ጊዜ የነገሥ ታትንና የነብያትን መጻሕፍት የዳዊትን መዝሙራትና የነገሥታትን ደብዳቤዎች ማሰባሰቡን ይገልጣል:: እነዚህን በነህምያ ቤተ መጻሕፍት የነበሩትን መጻሕፍት የኢየሩሳሌም አይሁድ በሶስት ክፍል ከፍለው ይጠቀ ሙባቸው ነበር::

1. ቶራህ/ሕግ/
2. ነቢአም /ነቢያት/
3. ካተቢም /ታሪክ/

ዕዝራና ነህምያ በሌሎች የአይሁድ ክፍሎች /ሳምራውያንና ኤሴያውያን/ እጅ የነበሩትንና ከነርሱ በኃላ የተጻፍትን መጻሕፍት አላሰባሰቡዋቸውም:: ስለዚህም በዕዝራና በነህምያ የተሰባሰቡት መጻሕፍተ ብሉያት የመጀመሪያዋ፡ የቀኖና መጻሕፍት መሆናቸው አስቀድሞ የታወጀላቸው ማለት ነው::

2. ሁለተኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (Deutrocanonical Books) እነዚህ መጻሕፍት ከዕዝራና ከነህምያ በኃላ የተጻፉ ወይም ቀጽመው ቢጻፉም በኃላ ተሰብስበወ ወደ ቀኖና የገቡ መጻሕፍት ናቸው:: እሥራ ኤላውያን በግብጽ በባቢሎንና በፋርስ በተደጋጋሚ በደረሰባቸው ስደት የተነማ ብዙ መጻሕት ተበታትነው ይገኙ ነበር:: በተለይም ከ2ኛው መ/ክ/ዘ በኃላ ወደ ቁምራን ገዳም /ሙት ባሕር አካባቢ / መሰባሰብ የጀመሩት ኤሴያውያን የያዙዋቸው መጻሕ ፍት ለብዙ ዘመናት ተበብቀወ ይኖሩ ነበር::

ከዚያ በኃላ በተነሡ የአይ ሁድም የክርስቲያንም ሊቃውንት እየተፈለጉ ሲገኙ ለቀኖና በመብ ቃታቸው ሁለተኛ የቀኖና መጻሕፍት ለመባል ችለዋል:: (Pope Shenouda III CD, Coptic orthodox church, Australia, 1988)

አንዳንድ ሰዎች እነዚህን መጻሕፍት «አፓክሪፋ» በማለት ለመጥራት ይሞክራሉ:: አፓክ ሪፋ የሚለው ቃል (Apocrypha) የግሪክ ቃል ሲሆን ሽሽግ ድብቅ ሥውር ማለት ነው:: ይህ ቃል ለጥንቆላ ለምትሐት መጻሕፍት ናልሆነ በቀር ከጥንት ዘመን ጀምሮ ታውቀው ለኖሩት ለመጻ ሕፍተ አምላካውያት የሚቀጸል አይደለም:: የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍት ከለሎች አሥራው መጻሕፍት ጋር የታሪክ ቅደም ተከተል ካልሆነ በቀር በምሥ ጢር በክብርም ትክክል ናቸው::

ለምሳሌ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን ሰዎችን በመቀበል ረገድ በምዕራብና በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በመጀመርዎቻቹ ሶስት መቶ ዘመናት ልዩነቶች ነበሩ በኃላ ግን የሂፓ/ 393 ዓ.ም/ እና የቅርጣግ ካርቴጅ

397 ዓ.ም ሲኖዶስ ጉባኤያት ካጸደቁት በኃላ በምዕ ራብም በምሥራቅም ከአሥራው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገብቶ በመቆጠር እኩል ተቀባይነት አግኝቷለ:: ይህ ማለት ግን በምሥጢርም በማዕረግም ከሌሎች ያንሣል ማለት አይደ ለም::/Pope Shenouda III CD,/

የዲዩትሮካኒንል መጻሕፍትን አሥራውነት በተመለከተ ማስረጃ

1. በ393 በሰሜን አፍሪን በሂፖ /Hipo/ ከተማ የተደረገው ሲኖዶስ የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥርን ሲዘረዝር የዲዩትሮካኖ ኒካል መጻሕፍትን ተቀብሏል::

2. በግሪክ ቋንቋ የተጻፋ ቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዞች /Codices/ መሆናቸው በሚታመነው
 - የቫቲካን ጥራዝ /Codex Vatican us /
 - የሲናይ ጥራዝ /Codex Sinaiticus /
 - የአሌክሳንደርያ ጥራዝ /Codex Alexander inus/ ውስጥ እነዚህ የዲዩትሮካኒንል መጻሕ ፍት ከሌሎች አሥራወ መጻሕ ፍት ጋር ይገኛሉ::

3. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቀደምት የሆኑት የቅድመ ኒቂያ /Anti Nicen Fathers/ እና ድኅረ ኒቂያ /Post Nicen Fathers/ የአሥራው መጻሕፍትን ተቀብ ለው ለሃይማኖት ማስተ ማርያ ለመሠረተ እምነት /ዶግማ/ ማስረጃ ለመናፍቃን መልስ መስጫ ተጠቅመ ውባቸዋል:: ከእነዚህ መካከል ዲዩናስዩስ ዘእስክንድርያ ሲፕ ርዩን ባስልዩስ ዘበቢይ ጎርጎርዩስ ዘኑሲስ ዩሐንስ አፈወርቅ ይጠ ቀሳሉ::

4. በሐዋርያት የቀኖና መጻሕፍት ውስጥ የተደነገጉት 85 ቀኖናዎች በ85ኛወ የተዘረ ዘሩት የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕ ፍትም ይገኛሉ::/El-satic Bin El-Assal the collection of canons chapter 2/

5. ትውፊታውያን አብያተ ክርስቲያናት ባገኙባቸወ መጻሕ ፍት ቁይር ግሪካውያን 76/77 ሮማውያን 72/73 ልዩነታቸወ እንደተጠበቀ ሆኖ የዲዩትሮ ካኖኒካል መጻሕትን ይቀበላሉ::

6. በበጥሊሞስ 2ኛ ጊዜ /285-246 ክክል በፊት / ሰባ ሁለት ሊቃናት ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ ሲተረጉሙ የዲዩት ሮካኖኒካል መጻሕፍትንም አብረው ተርጉመዋል::

7. የሐዲስ ኪዳን ጸሐፍት ለትምህርታቸው ማስረጃ ማጣቀሻ ምንጭ እያደረጉ ተጠቅ መውባቸዋል::

ጦቢት 4-15:- ለራስህ የጠላኸውን ለማንም አታድርግ::

ማቴ 7-12 ሉቃ 6-31 እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምት ወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲ አድርጉላቸወ ሲራክ2-16 እግዚአብሔርን የሚፈሩት ሰዎች ፈቃዱን ይፈጽማሉ ዩሐ 14-23 የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል::

ሲራክ 11-19 ያርፍ ዘንድ ተስፋ ባደረገ ጊዜ እበላለሁ እጠጣለሁ ባለ ጊዜ እንግዲህስ ደስ ይለኛል:: ገንዘብም በቃኝ ባለ ጊዜ የሚሞትበትን ቀን አያውቅም ገንዘቡን ሁሉ ለባዕድ ትቶ እርሱ ይሞታል::

ሉቃ 12-19 አንቺ ነፍሴ ለብዙ ዘመን ዕረፈ ብይ ጠጭ ደስም ይበልሽ እላታለሁ አለ እግዚአብሔር ግን በዚህች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስደት ይፈልጓታል:: ይህስ የሰበሰብከው ለማን ይሆናል? አለው::

ሲራክ 14-13 ሳትሞት ለባልንጀራህ በጐ ነገር አድርግ እጅህንም ዘርግተህ የተቻለህን ያህል ስጥ::

ሉቃ 16-9 የዓመጻ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሏችሁ በርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ::

ሲራክ 14-18 ቅጠለ ጭፍቅ ያለ ዛፍ የእንጨት ቅጠል የመጀመሪያው ቅጠል እንዲረግፍ ደማዊና ሥጋዊ ፍጥረት ሁሉ እንዲሁ ነው:: ይህ ይወለዳል ያ ይሞታል::

1ጴጥ 1-24 ያዕ 1-10 ሥጋ ሁሉ እንደሣር ክብሩም ሁሉ እንደሣር አበባ ነው ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግ ፈል::

ጥበብ 3-7 በክብር በሚጐ በኑበት ወራት ጻድቃን እንደ ፀሐይ ያበራሉ::

ማቴ 13-43 ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ

ጥበብ 13-1 እግዘአብሔ ርን የማወቅ አጕዳደል በልቡ ናቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ሰውነት ከንቱ ናቸውና:: በእነዚህ በሚታዩት ፍጥረቶች በዚህ ዓለም ያለ እርሱን ያውቁ ዘንድ ተስኗቸዋል::

ሮሜ 1-18:21 ስለ እግዚ አብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላ ክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና ስለዚህ እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመ ሰገኑት የሚያመካኙት አጡ::

ሄኖክ 1-9 ለወዳጆቹ ይፈርድላቸው ዘንድ እነሆ ከብዙ መላእክቱ ጋር ይመጣል ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችን ያጠፋቸዋል::

ይሁዳ ቁ 14 ከአዳም ጀም ሮሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ አዲፈርድ በኃጢአ ተኝነትም ስላደረጉት ስለኃጢ አተኛ ሥራቸው ሁሉ ዐመፀ ኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፍ ቅዱሳን ጋር መጥቷለ ብሎ ስለዚህ ትንቢት ተናገረ::

ተረፈ ኤር 7-3 የእሥራ ኤል ልጆች የተስማሙበት የክርስቶስን ዋጋ ሠላሳውን ብር ይቀበሉታል:: የሸክላ ሠሪ ቦታ ዋጋ አድርገው ይሰጡታል::

ማቴ 27-9 በነቢዩ በኤርሚያስ የተባለው የእሥራኤል ልጆችም አንዳንዶች የገመቱትን የተገመ ተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት የሚል ተፈጸመ::

ማቴ 4-7 ዩዲት 8-12 እግዚአብሔር ትፈትን ዘንድ አንተ ማነህ?

ዩሴፍ ወልደ ኩርዩን 4-59 ይሁዳንና ወንድሞቹን ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር በመሆን አንጥያኩስ 4ኛ ያረከሰውን ቤተ መቅደስ ያደሱበት በዓል በየ ዓመቱ እንዲከበር ወሰኑ::

ዩሐ 10-22 በኢየሩሳሌም የመቅደስ መታደስ በዓል ሆነ::

8. አሥራው መጻሕፍትን ምሉዕ አድርጐ ለመረዳት የግድ አስፈ ላጊ ናቸው:: አሪት ዘፍጥረትን በአሥራው መጻሕፍት ውስጥ ብናጣው ከመጀመሪያወ ፍጥረት እስከ ዩሴፍ ወልደ ያዕቆብ ያለውን ታሪክ ሁሉ እንደምናጣ ሁሉ እነዚህ የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍትን ከአሥራው መጻፍት ቁጥር በናወጣም ተመሳሳይ ጉድለት ይገጥመናል::

ለምሳሌ በዘፍ 3-1:5 የሰው ልጅና እንስሳት የሚግ ባቡት ቋንቋ እንደ ነበር ተገል ጧል:: የት ገባ? መልሱን የምናገ ኘው በመጽሐፈ ኩፋሌ ነው::

ኩፋሌ 5-8:17 በዚያችም ቀን እንስሳትና አራዊት ሁሉ ከዚህ ዓለም የሚመላለሰው ፍጥረትና የወፎች የሚንቀሳ ቀሰውም ፍጥረት ሁሉ አፍ በአንድ አንደበት ከመናገር ተከለከለ::

ዘንባባ ይዞ ማመስገን ሥርዓት አይሁድ ነበር:: ዩሐ12-12 ማን ጀመረው? ኩፋሌ 13-21 የሰሌኒ ጫፍ ለጋውን ያማረ የእንጨቱንም ፍሬ ይዞ በየቀኑ ዘንባባወን ይዞ ሰባት ቀን የመሠ ዊያውን ዙርያ ይዞር ነበር::

ዩዲ 15-12 ዩዲትም ሆሎ ፎር ኒስን ድል ባደረገችበት ጊዜ ዘንባባ ይዛ ዘምራለች::

2ዜና 33-18 የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ ጸሎት አቅርቦ ይቅር መባሉ በእሥራኤል የነገሥታት መጻሕፍት መጻፉ ተገልጧል:: እኛም ይህን በጸሎተ ምናሴ እናገኘዋለን::

ኤር 39-15፥18 በዚያ ቀን አድንሃለሁ:: ነፍስህንም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይ ፍ አትወድቅም ተብሎ ለኢትዮ ጵያዊው ለአቤሜሌክ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን ተረፈ ኤርምያስ 8-8 ያረጋ ጋጥልናል::

ታዲያ ይህ ሁሉ ከሆነ የዲዩትሮንኖኒካል መጻሕትን አይሁድና ፕሮቴስታንቶች ለምን አይቀበሉም?

1. አይሁድ

በ90 ዓ.ም በጃሚና ጉባኤ (Council of Jaminal) የተሰበ ሰቡት የአይሁድ ሊቃው ንተ የዲዩትሮካኒካል መጻሕፍትን ላለመቀበል ወስነዋል:: ለዚህም ዋናው ምክንያታቸው እነዚህ መጻሕፍት በግልጥ ቋንቋ ስለጌ ታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚናገሩ ነው::

*ዕዝ ሱቱ 4-1 መጀመሪያ በነብያት አድሬ ኋላ እኔ ሰው ሆኜ ሥጋ ለብሼ አስተምራለሁ አለኝ::*

*መቃ 1-1 ደያብሎስን ተበቅሎ የሚያጠፋ በኋላ ዘመን ወደነሣቸው ስለሚመጣ ክርስቶስ የግብፅን ሰዎች ደስ ይላቸዋል::*

*ሲራክ 24-10 በእርሱ ፈቃድ /በአብ/ በክበረ በማርያም ማኅፀን ሥጋን ተዋሐድኩ በምኩራብም አስተማርኩ::*

ተረፈ ኤር 11-51 በወለ ደው ልጁ አንደበት ፍሬን ያፈሩ ዘንድ ፈጣሪ እግዚአብሔር በፍጹም ተድላ ደስተ ደሴቶችን ይመርቃቸዋል:: እርሱም ራሱ ሰወ ሆኖ ያየሁት ከባሕርይ አባቱም ወደዚህ ዓለም የተላከ ሰው ሆኖም ወደዚህ ዓለም የመጣ እርሱ አበሯቸው ይታይ ዘንድ ይገለጥላቸውም ዘንድ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያትን ለእርሱ አገልጋዩች ሊሆኑ ይመርጣል::

ሌላው ምክንያታቸው ደግሞ ብዙዎቹ መጻሕፍት በዚያ ዘመን በግሪክ ተጽፈው በመገኘታቸውና የይሁዳ አይሁድ የግሪክ (Hellenistic judaism) አይሁድን ስለሚንቁ ያመጡት የክብር ማስጠንቀቂያ ነው::

የመጨረሻው ደግሞ እንደ መጽሐፈ ሄኖክና ኩፋሌ የመሳሰ ሉትን በወቅቱ ሊያገኛቸው ባለመቻላቸው ነው::

ከዚህ በተረፈ ግን በተለይ በእስክንድርያ የነበሩ የአይሁድ ሊቃውንት የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍትን እንደ ሰባ ሊቃናት ሁሉ ይቀበሏቸው ነበር::

2. ፕሮቴስታንቶች

ሉተረ ፕሮቴስታንቲዝምን ሲወጥን ተከታዩቹ ከወሰዷቸወ የመጀመሪያ ርምጃች መካከል ከግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ አይሁድ ወደሚቀበሏቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፊታቸውን መመለስ ነበር:: በዚህም የተነሣ የሰባ ሊቃናት መጻሕፍት በኃላም የዘመነ ሐዲስ የቤተ ክርስቲያን አበወ የተቀበሏቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሳይሆን በ90 ዓ.ም የአይሁድ ሊቃውንት የተቀበሏቸውን ብቻ እንቀበላለን ብለው ወሰኑ:: (Erdmans Bible Dictionary, 1987 P.552)

እንደ እውነቱ ከሆነ በ90 ዓ.ም የተሰበሰበው የአይሁድ ጉባኤ የተካኼደው በሁለት ፈታኝ ወቅታዊ ጉዳዩች ተወጥሮ ነበር:: የመጀመሪያው አይሁድ የራሳ ቸውን መጽሐፍ እየጠቀሱ መልስ ላስጧቸው የክርስቲያን ሊቃውንት መልስ ለመስጠት ትኩረት በሰጡበት ጊዜ ነው:: ይህም በመሆኑ በግልጥ ቋንቋ ነገረ ክርስቶስን ገልጠው የሚ ያስተምሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተቀብለው መልስ ማጣት አልፈ ለጉምና:: ሁለተኛው ደግሞ የአይ ሁድ ዳግማዊ የነፃነት እንቅስቃሴ 70 ዓ.ም ከፈነዳ በኃላ የብሔ ራዊነት ስሜት ያየለበት ጊዜ ነበር በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ፈርሳ የአይሁድ ሸንጎ /ሳንኻ ርዲን/ ሲሪጋ ተክቶ ይሠራ የነበረው የጃሚና ሳንኻርዲን ቤት ዲንታን ታይ ሸንጎ ስለነበር በ90 ዓ.ም በጃሚና ጉባኤ የመጻሕ ፍትን ቀኖና ለመወሰን የተሰባሰቡ አይሁድ በነበራቸው ፀረ ግሪካዊ አቋም በግሪክ ቋንቋ ብቻ ይገኙ የነበሩ መጻሕትን መቀበል አልፈለጉም::

በመሆኑም ከቤተ ክርስ ቲያን ሊቃውንት ይልቅ በዘመነ ክርስትና የተደረገን የአይሁድ ጉባኤ ውሳኔ መቀበላቸው ፕሮቴስታንቶችን ተረፈ አይሁድ ያደርጋቸው እንደሆነ እጂ ትክክለኛ መሥመር የያዙ አያሰኛቸውም::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

ዲ.ዳንኤል ክብረት

የቃል አስረጂዎች:- ዶ/ር ሐዲስ የሻነህ በቅድስት ሥላሴ መንፈ ሳዊ ኮሌጅ የዶግማና የቀኖና ቤተ ክርስቲያን መምህር
- ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዩ የሊቃውንት ጉባኤ አባለ

የጽሑፍ ምንጮች:- ፍትሐ ነገስት ንባቡና ትርጓሜው 1962 ዓ.ም
- ~~መጽሐፈ ሲኖዶስ ግጽው ጠቅላይ ቤተክህነት ቤተ መጻሕ ፍት ቁ139 1956 ዓ.ም~~
- ዲበኩሉ ዘውዱ ዶ/ር 81ዱ ቅዱሳት መጻሕፍ ምንጮች ቀኖናት 1987 ዓ.ም
- ዲበኩሉ ዘውዱ ዶ/ር ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና 1986 ዓ.ም
- The Coptic Encyclopedia, vol 2, p 456
- The Oxford Dictionary of the Christian Church, PP. 89-91